የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ጥቅምት 3 / 2005

# ግልፅ ደብዳቤ ለቀድሞ የወያኔ መሪዎች

ብዙዎቻችሁ የሕወኃት ከፍተኛ አመራር አባላት ነበራችሁናእንደምታወቁት ሁሉ የኢሕአፓድርጅት አመራር የነበሩና የቆዩ አባላትም በድርጅታችሁ እጅ በጎንደርና ጎጃም በሰኔ 1983 ወድቀው ወደ ባሕር ዳር ከተወሰዱ በኋላ ወደ ትግራይ ተጭነው ከዚያም ደብዛቸው ጠፍቷል ። ይህን እናንት አታወቁም ብሎ ማመኑ በጣም አስቸጋሪ ነው ።

ወደ ትግራይ ከተወሰዱም በኋላ ምን እንደረደሰባቸው የወያኔ ድርጅት የፖሊት ቢሮ/ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ/ የነበራችሁት አናወቅም ስትሉ የሚያምን ሊኖር መጠበቅ የለባችሁም ።
የፖሊት ቢሮ ወይም የድርጅቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ነበራችሁ ። የትግራይ ክልልፕሬዚዳን ት ነበራችሁ-- ምን የማተውቁት ነገር ነበረ? የመለስን ትዕዛዝ አስፈፃሚ ነበራችሁ ። የተገደሉም ከሆ ነ መለስ በራሱ በግሉ ሊገላቸው አይችልም--አለእናንተ ሙሉ ትብብር ። ለዚህም ነው እናውቅምን ት ታቸሁ ሀቁን አጋልጡ የምንላችሁ ። የሚያስብላቸው የሚያጨብላቸው ወገንም ይረፍ ሀቁን በማወቅ። ለምሳሌ የፀጋዬ ገብረ መድኅን-ደብተራው እናትና ታላቅ ወንድም የት ነው ምን ደረሰበት ሲሉና ሲ ጨነቁ ቆይተው ህይወታቸው አልፏል ። የሌሎቹም እስረኞች ቤተሰቦች በጭንቀትላይ እስከዛሬ አሉ ። ይገደሉ ብላችሁና አስገድላችሁም ከነበረ ይህንን በማመን ሀቁን ማጋለጥና ከሕዝብም ይቅርታ መጠየ ቅ ይኖርባችኋል ። ሌላ አማራጭ የለም ።
ምን እንንደረሰ አናውቅም ማለቱ ማንንም አያሳምንም ። ገለውናል ተጋድለናልም ማጠየቂያ ሊሆን አይችልም ። ዛሬም የወንጀለኛውን ድርጅት ምስጢር ምስጢራችን ብላችሁ እየደበቃችሁ ነው ማለት ነው ። ይህ ደግሞ አሳዛኝና የሚያስተዘዛብም ነው ። የወያኔ ፖለቲካ ተቃዋሚ ነን እያላችሁ የወያኔን ገበና፣ ምስጢርና ወንጀል መደበቅ ተባባሪና ተጠያቂ መሆን ነው ። ለዚህም ነው በወያኔ እጅ ወደቀው ደብዛቸው ስለጠፉት ሁሉ ሀቁን ተናገሩ ብለን ጥያቄ የምናቀርብላችሁ ።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE